በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ማናት?


## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com


*ቦታ፦* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ታህሳስ ፲፫ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.

# የሮማ ካቶሊክ “ቤተ ክርስቲያን”

ኢየሩሳሌም በ70 ዓ.ም. በጥጦስ ከወደመች በኋላ በኢየሩሳሌም የነበሩ አብያተ ክርስቲያናት ለጊዜውም ቢሆን ተዳክመው ነበር፡፡ በዚህም አጋጣሚ የሮም ጳጳሳትና አስተዳደርም ወደ ኢየሩሳሌም ለመስፋፋት ዕድል አገኙ፡፡

በየጊዜው የተፈጠሩ ፓለቲካዊ ሁኔታዎች የሮም ጳጳሳትና ፓፑ በዓለም የተለያዩ ክፍሎች ተፅዕኖ ማሳደር እንዲችሉና በዚህም እንዲቀጥሉ ዕድል ፈጥሮላቸዋል፡፡

ከአራተኛው እስከ ስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመንም በቢዛንታየን የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትን ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን ሁሉ ተቆጣጠሩ፡፡ የሮምም ጳጳሳት በዓለም ያሉ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ጠበቆች አድርገው ራሳቸውን ቆጠሩ፡፡ «ሮም የቅዱስ ጴጥሮስ መንበር ስለሆነች የሮሙ ፓፓ የሁሉም ራስ ከተማዋም የክርስቲያኖች ማዕከል ናት፡፡»ብለው ማወጅ ጀመሩ፡፡

እያደርም «ያለ ሮማ ማንኛውም ሃይማኖታዊ ውሳኔ ተቀባይነት አይኖረውም» አሉ፡፡ አያይዘውም በ451 ዓ.ም. ምስራቃውያን መለካውያንን ይዘው የንስጥሮስን ትምህርት በማሻሻል ንጉሳቸው መርቅያንን ለማስደሰት ጥንታውያኑን አብያተ ክርስቲያናት በማግለል ለብቻቸው በኬልቄዶን ጉባኤ አድርገው «ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ አካል ሁለት ባሕርይ ነው» ብለው ውሳኔ ወሰኑ፡፡ ይህም ውሳኔአቸው በዮሐ 10፡30 ከተጻፈው ጋር ይጋጫል፡፡

# <u>የሮማ ካቶሊክ "ቤተ ክርስቲያን"</u>

አንዲቱንም ቤተ ክርስቲያን ትተው ለብቻቸው ምስራቃውያን ኦርቶዶክስን (ግሪክ ሩሲያ...) አስከትለው ወጡ፡፡ እነዚህም የምድራዊውን ንጉሥ ፈቃድ ለመፈጸም በሥጋ ሀሳባቸው ተጉዘዋልና ጉባኤያቸው «ጉባኤ ከለባት» እነርሱም «መለካውያን» ይባላሉ፡፡

በዚህ ጉባኤ ቀዳምያኑ ኦርየንታል ኦርቶዶክሶች (ግብጽ፤ ሶርያ፤ ሕንድ፤ አርመን፤ ኢትዮጵያ) አልተሳተፉም፡፡ መለካውያኑ አባቶቻችንን አስገድደው የውሳኔያቸውን አሳብ እንዲቀበሉ ለማድረግ ሞክረው ነበር፡፡ የግብጽ ፓትርያርክ እንደነበረው እንደ ዲስቆሮስ ያሉትን ጥርሳቸውን በመንቀል ጽሕማቸውንም በመንጨት አንዲቱን፣ ሐዋርያዊቱን፣ ቅድስቲቱንና፣ ዓለም አቀፋዊቱን ቤተ ክርስቲን በምድራውያን ነገሸታት ሐሳብና ፈቃድ ሳትበረዝ ትምህርቱና ትውፊቱ ተጠብቆ ቺንዲኖር አድርገዋል፡፡

«*እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- በመንገድ ላይ ቁሙ ተመልከቱም የቀደመችውንም መንገድ ጠይቁ መልካሚቱ መንገድ ወዴት እንደ ሆነች እወቁ በእርስዋም ላይ ሂዱ ለነፍሳችሁም ዕረፍትን ታገኛላችሁ እነርሱ ግን አንሄድባትም አሉ፡፡*» <u>*ትን ኤር 6፡16*</u>

በሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረው የሮሙ ፓፕ አራፎን አልተቀበሉትም እንጂ «የሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ መንበር ነንና ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት የሮማን አለቅነት ወይም ራስነት እንዲቀበሉ ጥያቄ አቅርቧል፡፡ በስምንተኛውም መቶ ክፍለ ዘመን የነበረው ፓፕ ስቴፋን «እኔ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ነኝ... በእግዚአብሔር ፈቃድ የዓለም ብርሃን ሆኜ ተልኬላችኋለሁ...» ብሎ ነበር፡፡

# <u>የሮማ ካቶሊክና ምስራቃውያን ኦርቶዶክሶች</u>

**እስካሁን ያየነው የሮማውያንን እንቅስቃሴ ቢሆንም ምስራቃውያኑ ከሮም ካቶሊክ ሳይለዩ በሁሉም እየተባበሩ መቆየታቸውን ነው፡፡ በዚህም ሁኔታ እስከ 1054 ዓ.ም. ድረስ ከቆዩ በኋላ በመጨረሻ በ1054 ዓ.ም. ተለያዩ፡፡ ለመለያየታቸውም ምክንያት የሆናቸውም የሮማ ካቶሊክ የጨመረቻቸው እንግዳ ትምህርቶች ናቸው ይላሉ፡፡ እነዚህም እንግዳ ትምህርቶች፡-**

ሀ. በጸሎተ ሃይማኖት ላይ መንፈስቅዱስን ከአብና ከወልድ የሠረጸ ነው ማለታቸው፡፡ ***<u>ዮሐ 15፡26</u>*** ግን መንፈስ ቅዱስ ከአብ የሠረጸ ነው ይለናል፡፡

ለ. የሮም ፓፕ አይሳሳትም የሁሉም አለቃ ወይም ራስ ነው ማለታቸው ፡፡ ይህን ትውፊተ ቤተ ክርስቲያንም ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ አይደግፈውም፡፡

ሐ. ድንግል ማርያም ከአርያም የመጣች ናት ማለታቸው፡፡ ነገር ግን ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ዘር የተቆጠረለት በእመቤታችን የተነሳ እንደሆነ ልብ እንበል፡፡ ***<u>ማቴ. 1፡11</u>***

**«የሮም ፓፕ አይሳሳትም የሁሉ አለቃ ወይም ራስ ነው» በማለት ለሚያነሱት የሚያቀርቡት ምክንያት <u>በማቴ. 16፡18</u> «አንተ ጴጥሮስ ነህ፤ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፡፡» በማለት የተነገረውን ነው፡፡ ትርጉሙም ኢየሱስ ክርስቶስ የባህርይ አምላክ ነው በማለት ቅዱስ ጴጥሮስ በሰጠው ምላሽ እንደተገለጠው ቤተ ክርስቲያን በኢየሱስ ክርስቶስ መሠረትነት ላይ ትታነጻለች ማለት ቢሆንም እነሱ ግን በራሱ በጴጥሮስ ላይ አጥንቱ ተከስክሶ ደሙ ፈሶ ለማለት መፈለጋቸውን ካለመገንዘባቸው በላይ ለሚሉትም በቂ ማገናዘቢያ ምንጭ የላቸውም፡፡**

# <u>የሮማ ካቶሊክና ምስራቃውያን ኦርቶዶክሶች</u>

**ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስን አለቃቸው አድርገው አልሾሙትም። በ51 ዓ.ም. በኢየሩሳሌም በተደረገውም የሐዋርያት የመጀመሪያ ሲኖዶስ ሰብሳቢው ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ ነበር። <u>የሐዋ ሥራ 15:1-41</u>**

**የቅዱስ ጴጥሮስን ሥልጣን በተመለከተ እጁን በመጫን አገልገሎቱን የፈጸመው በሮም ብቻ ሳይሆን በእስክንድርያ በአንጾኪያና በሌሎችም ጭምር ነበር። ሮማውያን ራሳቸውን ቁልቁል ከሰቀሉት ከቅዱስ ጴጥሮስ ጋር በማገናኘት ራሳቸውን የበላይ አድርገው የቆጠሩት ለሥልጣን ከነበራቸው ጥማትና ከአንዲቱም ቤተ ክርስቲያን አስቀድመው ከመለየታቸው የተነሳ ነው። ይህም ትምህርት በአንዲቱ ቤተ ክርስቲያን አስቀድሞ ያልነበረ እንግዳ ትምህርት ነው።**

**ፖፑ የጴጥሮስ ምትክ ነው፣ አይሳሳትም የሚሉትንም በተመለከተ ራሱ ጴጥሮስ ችን ከደችማ ሐሳቡ የተነሳ ንስሐ ሳይገባ አስቀድሞ በጌታችን የተገሰጸ ሆኖ በመገኘቱ ቃሉንም ለመጠበቅ አለመቻሉንም መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናል። <u>ማቴ 16:23 ፣ ማቴ 26:34-35 ፣ ማቴ 26:69-75።</u> እግዚአብሔር ካላገዘው በቀር በእግዚአብሔር ፊት እንኳን አርአያው ወደ ጥፋት የሚመራው ሰው ሰማያትም ንጹሐን አይደሉም። <u>ኢዮብ 15:15።</u>**

**ይህ የመለካውያን የተሳሳተ ከሥልጣን ከጥቅም ጋር የተቆራኘ አካሄድ በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ለሉተር መነሳት ምክንያት ሆኗል።**

# የኦርቶዶክስ ተዋሕዶና የሮማ ካቶሊክ ልዩነት

በሮማ ካቶሊክ ከትውፊተ ቤተ ክርስቲያን የወጣ የተሳሳተ መንገድ የተነሳ የምንለያይባቸው የእምነት መሠረቶች ወይም ትምህርቶች

1. የኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት - አንድ አካል ሁለት ባሕርይ ነው ይላሉ።
2. የመንፈስ ቅዱስ የባሕርይ አምላክነት - ከአብና ከወልድ ሠረጸ ይላሉ።
3. የፓፕ አለመሳሳት - ፓፕ አይሳሳትም ይላሉ።
4. እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም - ኃይለ አርያማዊት ናት ይላሉ።
5. ቅዱስ ጴጥሮስ - የሐዋርያት አለቃ ነው ይላሉ።
6. የተሳሳተ ትውፊት - ከጥንቱ ትውፊት የተለየ አቅጣጫዎች አሉአቸው።
7. ጾም - በጾም ወቅት ወተትና የሚመስሉትንም ይጠቀማሉ።

## *በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን*

1. ሁሉም የቤተክርስቲያን ምስጢራት የሚፈጸሙት በጳጳሳትና በቀሳውስት ብቻ ነው።
2. ሥጋውን የሚያቀብለው ቄሱ ወይም ኤጲስ ቆጶስ ሲሆን በዕለት የተሰዋው መሥዋዕት አያድርም። ***ዘጸ 12 :10***
3. ምስጢረ ሜሮን ከጥምቀት ቀጥሎ ወዲያው ይፈጸማል።
4. ቤተ ክርስቲያን ትውፊታዊትና መጽሐፍ ቅዱሳዊት ናት ።
5. ኦርቶዶክሳውያን መጋባት የሚችሉት ከኦርቶዶክሳውያን ጋር ብቻ ነው። ***ነህምያ 13 :27***
6. በዝሙት ከሆነ ምክንያት በቀር መፍታት አልተፈቀደም። ***ማቴ 5:32።***
7. ቅዳሴ ከጥንት እንደነበረው በዓለሙ ሁሉ ተጠብቆ ይኖራል።
8. በቀን ከአንድ ጊዜ በላይ በመንበሯ አይቀደስም።

# የኦርቶዶክስ ተዋሕዶና የሮማ ካቶሊክ ልዩነት

## *በሮማ ካቶሊክ*

1. ጥምቀት ተክሊልና ቅዱስ ቁርባን በዲያቆናት ይፈጸማሉ:: ሌሎቹ ምስጢራት (ቀንዲል፤ ንስሐ፤ ክህነትና ሜሮን) ግን በቀሳውስትና በካርዲናሎች ይፈጸማሉ:: ይሽም የጥንትዋ ቤተ ክርስቲያን ትውፊት አይደለም::
2. *ሥጋውና ደሙን የሚቀበሉ ቀሳውስት ብቻ ናቸው:: ምዕመናኑን ግን ሥጋውን ብቻ ያቀብሉአቸዋል:: ይህም ከዮሐ 6:54 ጋር ይለያያል - ሥጋዬን ብሉ ደሜን ጠጡ አለ እንጂ ሥጋዬን ብቻ አላለም::*
3. *መሥዋዕቱን አዘጋጅተው እያስቀመጡ - እያዋሉና እያሳደሩ ያቀብላሉ:: ይህም ትውፊት የቤተ ክርስቲያን አይደለም::*
4. ካቶሊካውያን ካቶሊካዊ ያልሆኑትን ሊያገቡ ይችላሉ - ይፈቀድላቸዋል::
5. ፍቺ በዝሙትም የተነሳ ቢሆን ፈጽሞ አይፈቀድም:: *ማቴ 5:32* ግን በዝሙት ከሆነ ብሎ ያስረዳል::
6. ቁርባኑን ሴቶችም እንዲያቀርቡ ይፈቀድላዋል:: ወንድም ሴትም ያለ ክህነት ያቀርባሉ::
7. በአንድ መንበር ከአንድ ጊዜ በላይ ይቀድሳሉ::
8. በልተው ጠጥተው ይቀድሳሉ ይቆርባሉ ያቀርባሉ::
9. *መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ የሠረጸ ነው ይላሉ:: ዮሐ 15:26 ይህን አይልም::*
10. *ድንግል ማርያም አባትና እናት የላትም:: ይህን መጽሐፍም ትውፊትም አይልም::*
11. *ፓፑ አይሳሳትም፣ ሮም የክርስትና ማዕከል ናት፤ ቅዱስ ጴጥሮስ የሐዋርያት አለቃ ነው::ነገር ግን ማቴ 16:23 ማቴ 26:34-35 ማቴ 26:69-75 የሐዋ ሥራ 15:9 አይሉም::*
12. በጾም ወተት መጠጣት... ይቻላል:: *ነገር ግን ይህ በትውፊትም በመጽሐፍም አልተፈቀደም:: ሕዝ 4፤1-ፍጻሜ::*

# ይቀጥላል...

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org